ሰኔ 1 1999(ጁን 7/ 2007)

## በቅሎ አባትሽ ማነው ቢሏት ፈረስ አጎቴ ነው አለች

(ከአያልነሽ)

ሰሞኑን የወያኔ ቁንጮ የሆኑ ዋና ዋና ሰዎች ግንቦት 20 (ዘመነ ውጥረትን) ምክንያት በማድረግ ከምኒልክ ቤተ-መንግሥት ሆነው ለእኛ በውጭ ለምንገኘው ኢትዮጵያውያኖች፣ ሊነገረን የሚገባውን አዋጅ ለመንገር ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል። የወያኔ/ህወሃት ወላጅ የሆኑት ሁለት ቱባ ቱባ የወያኔ አለቆች በወያኔ ሲቭሊቲ ሩም(ክፍል) ተጋብዘው የቀረቡት አባይ ጸሃዬና ስብሃት ነጋ ሲሆኑ ሁለቱም የወያኔ መስራቾች "የትምክህተኞች" መዲና ከሆነችው ከአዲስ አበባ ነበር በሲቭሊቲ ሩም(ክፍል) አማካኝነት ውጭ ካለው "ትምክህተኛ ኢትዮጵያዊ" ጋር ሊያገናኙአቸው የሞከሩት። እነኝህ የወያኔ አለቃዎች በተለያየ ጊዜ ይቅረቡ እንጅ ሁሉቱም የቀረቡበት ሰበብ ግን ግንቦት 20 (ዘመነ ውጥረትን) ምክንያት በማድረግ መጋበዛቸውን የሲቪሊቲ ሩም ዋና አዝዥ የሆነው የፓልቶኩ አባመላ (አቶ ብርሃነ) ሲያስተዋውቅ ተሰምቷል። ይህንን በሲቪሊት ፓል ቶክ ክፍል ውስጥ የታወጀውን አዋጅ የወያኔ ነጋሪት ጋዜጣ የሆነው አይጋ በድረ ገጹ ላይ ለጥፎቷል። የሁለቱንም ግለሰቦች የሲቪሊቲ ሩም ቀይታን አይጋ ቢለጥፈውም፣ እኔ ከአይጋ ፎረም ድረ ገጽ ላይ የስብሃት ነጋን የእብሪት አዋጅ ወስጄ የጽሁፌ እምብርት አድርጌዋለሁ።

የተከበራችሁ አንባቢዎቼ ሆይ!
በዚህ የስብሃት ነጋ የእብሪት አዋጅ ላይ ለመጻፍ ስነሳ አነሳሴ ይህ የወያኔ ቡድንና የቡድኑ ዋና ዋና ቁንጮ የሆኑ ጨካኝ ባለሥልጣኖች፣ ምንጊዜም ቢሆን በአነሳሳቸውና በአፈጣጠራቸው (ዛሬም ብዥታ የሚኖራቸው አንዳንድ የዋህ የሆኑ ግለሰቦች ካሉ) የተከበረውን የኢትዮጵያን ህዝብ በአጠቃላይ፣ እንዲሁም የተከበረውን የትግራይ ህዝብ በተለይ ሊያዋርዱና እንዲያፍር ለማድረግ የተላኩና የመጡ ጉግማንጉጎች ለመሆናቸው ስብሃት ነጋ ዛሬም በእብሪት አዋጅ አረጋግጦልናል። ይህ የስብሃት ነጋ ያልተቀየረና የኖረ የእብሪት አቋም፣ ከኃይለኛ ድንፋታ ጋር ተቀላቅሎ በተለይም በውጭ አገር ለሚኖሩ የትግርኛ ተናጋሪ ማህበረሰብ በተለይ፣ ከወያኔ ዘንድም "እርቅ" በመጠበቅ ለባዘናችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖች ሁሉ በአጠቃላይ፣ ለአንዴና ለሁሌም እርማችሁን እናድታወጡ የተሰጠ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ነው። ስብሃት ነጋ በ70 ዎች የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ አዛውንት ሲሆን፣ አለመታደል ሆኖ እንደ ስብሃት ነጋ ያሉ የእድሜ ባለጸጋዎችን እንደ እድሜያቸው አልሆን፤ አልሰክን እያሉ ራሳቸውን ሲያስገምቱና ያዙን ልቀቁን እያሉ ራሳቸውን ሲያቀሉ በተመለከተ ቁጥር፣ የሀገራችን የኢትዮጵያ ህዝብ እድሜያቸውን አጉል ነው፣ ቁጥር ነው ለማለት "የእንጨት ሽበት" ሲል ይገልጻቸዋል። የ70 ዓመቱ ሰው ስብሃት ነጋና ድርጅቱ ወያኔ፣ ይህንን ኩሩና ስልጡን ህዝብ ነው እንግዲህ ነፍስ ከአወቁ ጀምሮ ይሄው እስከዛሬ የሽምግልና እድሜያቸው ድረስ እየሰደቡና እያዋረዱ

ቀጥቅጠ ለመግዛት ቆርጠው የተነሱት። ለእኔ ምክንያታቸው ይገባኛል። ደካማ የሆኑና በራሳቸው ላይ የማይተማመኑ ሰዎችን የሚፈታተኑ ሁለት ከባድና መድሃኒት የማይገኝላቸው በሽታዎች <u>የዝቅተኝነት ስሜትና የማንነት ቀውስ</u> በመሆኑ ለአፍታም ቢሆን በወያኔ መሪዎችና ፈጣሪዎች ላይ ጥያቄ ኖሮኝ አያውቅም። ግን ወያኔን ከትግራይ ህዝብ ጋር ለማያያዝና ወያኔን የትግራይ ህዝብ ኩራት አስመስለው ሊያስረዱንና ሊያሳምኑን የደከሙና የሚደክሙትን ግን መልሱን ''አቦይ'' እያሉ ያነገሱት ስብሃት ነጋ ለራሳቸው በሲቪሊቲ ሩም ውስጥ እቅጩን የነገሩቸውና የነገረን ይመስለኛል። ስለዚህ ይህንን ኩሩና የታሪካችን እምብርት የሆነውን የትግራይን ህዝብ፣ በነዚህ በወያኔ ጉግማንጉጎች የተጠነሰሰለትን የጥፋት ደባ ተገንዝበን፣ ከተጠነሰሰለት የጥፋት ደባና ከታጠረበት የእሾክ አጥር እንዲወጣና ከቀሪው ኢትዮጵያዊው ህዝብና ወገኑ ጋር ሃዘኑም ደስታውም የጋራው ነውና በጋራ የሚያደርግበትን መንገድና ቀዳዳ እናመቻችለት ዘንድ በአጠቃላይ በኢትዮጵያዊው በተለይ ደግሞ በውጭ በሚገኘው የትግርኛ ተናጋሪው ማህበረሰብ ላይ ከባድ ሃላፊነት ወድቆብናል።

የተከበራችሁ ውድ አንባቢዎቼ ሆይ! የስብሃት ነጋ የጁን 1/ 2007 በሲቪሊቲ ፓልቶክ ሩም(ክፍል) ውስጥ የተነገረውን አዋጅና አባ መላ ታሪካዊና ዶክመንተሪ ቃለ መጠይቅ በማለት አወድሶ በድረ ገጾች ላይ እንደሚለጠፍልን የነገረን ይህ የእብሪትና በድንጋጤ  ውስጥ የሚገኙ አምባገነኖች የሚያሰሙት የፍርሃት ጩኸት፣ በርግጥም ታሪካዊ አዋጅና እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በተቻለ መጠን ቀርጾ/ገልብጦ በእጁ ሊያስገባው የሚገባ ሰነድ ነው። እባካችሁ! በድምጽ በአይጋ ላይ በአማርኛ በ4 ክፍል ተከፍሎ የተለጠፈውን ይህ የስብሃት ነጋ ''የእንደመሰሳችኋለን'' የእብሪት አዋጅ በእጃችሁ እንድታስገቡት ከታላቅ አክብሮት ጋር በትህትና እጠይቃለሁ። የስብሃት ነጋ የእብሪት አዋጅና ድንፋታ ያስታወሰኝ የካቲት 14 /1983 ዓ.ም እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር መንግስቱ ኃ/ማርያም ለኢትዮጵያ ህዝብ በሞላ፣ በትዕዛዝ እንዲሰማው ተደርጎ በሬድዮና በቴሌቪዥን ጎራዴ እየመዘዘ ያስተላለፈውን የመጨረሻ ቀን የመሰናበቻ እሪታን ነው። መንግስቱ ኃ/ ማርያም ይህንን የመጨረሻ የእሪታ ንግግሩን አድርጎ ለእኛ የስንብት፤ ለእርሱ ግን የሚቆይ መስሎት ከደነፋ በኋላ በሶስተኛው ወር፣ ግንቦት 20 (ዘመነ ውጥረት ወያኔን ይዞ) ወያኔ ኢህአዴጋዊ ድሪቶውን ለብሶ ከትግራይ አዲስ አበባ በተመቻቸለት መንገድ፣ ለኢትዮጵያ ህዝብ እኔ የማላውቃችሁ እናንተ ግን የምታውቁኝ በማለት ምኒሊክ ቤተ መንግሥት ውስጥ ገባ። የታሪክ አጋጣሚ ይሉዋል ይሄ ነው! ስብሃት ነጋና ድርጅቱ ወያኔ፣ ዛሬ ከአዲስ አበባ ሆነው በውጭ ለምንኖረው ኢትዮጵያውያኖች በሲቪሊቲ ሩም ቪዛ አልፈው ወደእኛ የደረሱት፣ ''መንግስት'' እየመሰሉዋችሁ ''መንግስታዊ ፕሮቶኮል'' ስትሰጡ ለከረማችሁ ወገኖቼ ሁሉ እያዘንኩ፣ እነ ወያኔ እንደ ድርጅት ይህ እድል ቢያጋጥማቸውም የመንግስትነቱን ወግ ግን እነሆ እስከዛሬ አልተላመዱትም። መንግስታዊ ወግ ልታላብሱዋቸው ለሞከራችሁ ሁሉ ለድካማችሁ አሁንም በድጋሚ አዝናለሁ! ተወዳጁ ጳውሎስ ኞኞ ነፍሱን ይማረውና እንደገቡ በምኒሊክ ቤተ መንግስት ውስጥ ሰፍረው መንግስት ነን እያሉ የሚሰሩትና የሚያደርጉት ነገር ሁሉ ግን ግራ ቢያጋባው ተጨንቆ በጊዜው በዚያ ለዛ ባለው አቀራረቡ <u>መቼስ መንግሥት ከሆናችሁ አይቀር</u> ብሎ፣ በአቅሙ እንደ አገርና እንደዜጋ

በመቀርቀር የኢትዮጵያን ህዝብ እንዳያዋርዱ፤ እንዳያሳፍሩ ብሎ ሊመክራቸው ሊዘክራቸው ሞክሯል። ጋሽ ጳውሎስ በጊዜው ለብዙዎቻችን ቀላል የመሰሉን ነገሮች ለእርሱ ግን በእድሜው ከወያኔ በፊት ቢያንስ ሁለት የመንግስት አስተዳደሮችን በአካል በህይወት ኖሮ የተመለከተና ያሳለፈ ነበርና፣ በኢትዮጵያዊነት ባህልና ታሪክ ተኮትኩቶ ለአደገ ኢትዮጵያዊ ግን እንደ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሚያሳፍሩ መስሎ የሚታዩ ድርጊቶቻቸውን ሁሉ በቅንነት በብዕሩ ሊያስተካክል፣ ሊሞርድ ተጣጥሯል። ጋሼ ጳውሎስ ወያኔዎች አዲስ አበባ በገቡ ጊዜ ለአጭር ጊዜም ቢሆን በህይወት ነበርና በዚያች በነበረበት የህይወት ጊዜው ውስጥ እነኝህን ሰዎች ሰው መስለውት ከመጨነቅ ነበር ጭንቀቱን በብዕሩ ሊያሳያቸው የሞከረው። በእሱ ቤት እንደ እንግዳ ቀጥሮ እንደ ቅርብ ዘመድና ቤተሰብ፣ ወገኖቼ ናቸው ብሎ በመጨነቅም፣ የበኩሉን እንደ አገር እንደ ዜጋ ሊያደርግ ጣረ። ያኔ እንደገቡ ሰሞን በቤተ-መንግስት ግቢ አጥር ላይ ሳይቀር ያጠቡአቸውን ልብሶች ያሰጡ ነበር ሲባል ብዙዎቻችን በጊዜው እንደቀልድ እየቀጠርናቸው እየሳቅን ያሳለፍናቸው ድርጊቶች ቢሆኑም፣ በወያኔ ግን ሲደረጉ የነበሩና የቀዩ ናቸው። ዛሬም ቢሆን ከዚያ ያልወጡና የማይመጥናቸውና የማያውቁት ነገር ጥሎባቸው ቢያገኙትም ሊያበጃጁት አልቻሉም። እንድ የእኔ ቢጤ፣ ሎተሪ ይጫወትና፣ ለቁጥር የሚያታክት ገንዝብ ደረሰው እንበል። ገንዘቡን ያገኘው ድንገት በሎተሪ ጨዋታ ነበርና ያ ለቁጥር የሚታክተው ገንዘብ ዋጋውን አያውቀውምና እስከ መቼም የሚያልቅ ስለማይመስለው፣ ያ በሎተሪ ጨዋታ የተገኘው አታካች ገንዘብ የትም እንዳገኘ ይበትነዋል እንበል፤ ያለ እቅድ ስለሚወጣ። ያ በሎተሪ የተገኘ ለቁጥር የሚያታክተው ገንዘብ፣ ሲገኝም በድንገት ነውና ሲጠፋም ሆነ ሲያልቅ (መጥፋቱም ሆነ ማለቁ) እንደዚያው ሁሉ ድንገተኛ ይሆናል። ግን ሙጥጥ ብሎ አልቆ ባዶ እጁን መቅረቱን የሚያውቀው ገንዘቡ በእርግጥም ከአለቀ በኋላ ነው። ወያኔዎችን እንደዚህ ሎተሪ ተጫዋች አድርጌ እመለከታቸዋለሁ። ለዚህም ነው "አነስተኛ ሀብት በትጋት ሲገኝ ትልቅ ሀብት ግን ዕድል ይጠይቃል።" የሚባለው።

የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ! ስብሃት ነጋ በጁን 1/2007 የሰቪሊቲ ቀይታው በሩሙ(ክፍሉ) ውስጥ በተገኙት እድምተኞች፣ በርካታ ወይም ብዙ ሰዎች ለጥያቄ እጅ ማውጣታቸውን የሩሙ አስተናባሪ የሆነው አባመላ (አቶ ብርሃነ) ሲናገር ይደመጣል - አይጋ ላይ በተለጠፈው የስብሃት ነጋ የአዋጅ ጥሪ ላይ። ይህንን የስብሃት አዋጅ በሙሉ አይጋ ላይ አዳምጨዋለሁ። ከመጀመሪያው ጀምሮ የስብሃት ነጋን ንግግር ላዳመጠ ሰው አዋጁ ራሱን ስብሃት ነጋን፣ ተብትቦ የሚጥል ለመሆኑ ንግግሩን ያዳመጣችሁት በሙሉ ልትፈርዱ ትችላላችሁ። ለዚህም ነው በወያኔ የሲቪሊቲ ፓልቶክ ሩም ውስጥ የተኮለኮሉትን በአብዛኛው የወያኔ ደጋፊ የሆኑ ሰዎችን በሙሉ አስቆጥቶ አባመላን ፋታ እስኪያሳጣው ድረስ የጥያቄ እጆች ብዛት እንዳስጨንቁት ያመላከተን። ይህንን እውነታ እንዳለ ያለማጋነን የሰማሁትን ያስቀመጥኩ ለመሆኑ ትረዱልኝ ዘንድ አሁንም በድጋሚ በአይጋ የተለጠፈውን የአባመላን ጭንቀት አዳምጡት። ወደ ቁም ነገሬ ልመልሳችሁ። ስብሃት ነጋ ዛሬ ለምን ይህንን አዋጅ ሊያውጅ ተገደደ? የወያኔ ቱባ ቱባ ባለስልጣኖች በዚህ ሰሞን 70 ሚሊዮን ህዝብ አስረው በሽብራቸው ውስጥ አስገብተው እያለ ከ70 ሚሊዮን ህዝባችን አንጻር በጣም በጣም ጥቂት

ለሆነው በውጭው ዓለም ለሚኖረውና ለሚያናንቁት ኢትዮጵያዊ፣ እንደእነ ስብሃትና አባይ ጸሐዬ ያሉ የወያኔ አለቆች መጥተው ”ጸጥ በሉ አሊያ በቅልጽምና” የሚል አዋጅ ለመንገር ለምን አስፈለገ? ምንስ ተፈጠረ? ወዘተ........ ብዙ ማለት ይቻላል። ወያኔን ለምናውቀው ጉዳዩ ውስብስብ ያልሆነና ለምን ይሆን? የሚያሰኝ አይደለም። ውስብስብ አለመሆኑን ደግሞ የወያኔው መስራች ስብሃት ነጋ የሚያውቀው ይመስለኛል። ”አቦይ” የሚል ቅጽል ስም ያላበሱት የሻቢያ ተጋዳሊቲዎች፣ ዛሬ በነስብሃት ነጋና በወያኔ አጋፋሪነት የደረሳባቸውን መከራና የኤርትራ ህዝብ እንደ ሕዝብ  የተቀበለውን ፍዳ ስናይና ስናስበው፣ ጎሽ እሰዬው እንኰዋን ሆነ፣ የተመኘውን አገኜ የምንል ጨካኞች ሳንሆን፣ በዕውነቱ እኛ ኢትዮጵያውያኖች ወገናችን ለሆነው የኤርትራ ህዝብ አውቆትም ሆነ ሳያውቅ አሁን ላለበት መከራ መዳረጉና መብቃቱ፣ በእጅጉ የሚያስዝነንና የምናዝንለት ነን። ይህንን ጭካኔና እሰዬው! እንኳንም ቀመሰ ብሎ በስቃያቸውና በመከራቸው ለመሳለቅ መሞከር የወያኔን ጨካኝ መሪዎችን ባህርይና ክፋት መላበሰን ይጠይቃል።  ለዚህም ነው ስብሃት ነጋ በእብሪት አዋጁ በተደጋጋሚ በማስረገጥ የነገረን - ”ህገ-መንግስታችንን የተዳፈረ” የመጀመሪያው ቀዳሚ እርምጃ ሊሆን የሚችለው ይልና ”የትግራይ ህዝብ ተገንጥሎ ወደ ኤርትራ” ይቀላቀላል የሚል ነው። ይህም አባባሉ ከ1968ዓ.ም (እንደ ኢትዮ አቆጣ) ጀምሮ በወያኔ ታስሮ የሚገኘውን ኢትዮጵያዊውን የትግራይ ህዝብ፣ እንደ መያዥ ይዞ በሰቀቀን ውስጥ እንድንኖር የሚያደርግ የወያኔ የጭካኔ አላማ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። የወገናችን የትግራይ ህዝብ ሰቀቀን ደግሞ ያመናል። እንዴት አይመመን? ወገናችን የትግራይ ህዝብ በወያኔ እንደ መያዥ መያዙ ያስጨንቀናል። እንዴት አይስጨንቀን? ስብሃት ነጋም ያልካደው እውነታ በ17 ዓመቱ ከደርግ ጋር ባደረጉት ጦርነት ከባዱ ዘመን ያለው ያ መሆኑን ሊናገር ተግዱዋል። እርግጥ ነው ወደ አዲስ አበባ ሲገስግሱ ወያኔዎች ትግራይ ውስጥ በነበሩበት ወቅት ያደረጉት ጦርነት ይበዛ እንደነበር ስብሃት ነጋም አልካደም። ግን በትግራይ ውስጥ የትግራይን ህዝብ ሳይወዳቸው ምሽግ አድርገውት፣ ራሳቸው ወያኔዎች በየአቅጣጫው በሚለኩሱት ጦርነት ሁሉ ያ ህዝብ እንዴት ሊያመልጥ እንደሚችል አይገባኝም። ባደረጉት ጦርነት ሁሉ ስብሃት ነጋ እንደገለጸው ከደርግ ጋር ብቻ ሳይሆን ከሁሉም ጋር ይናከሱ ነበርና (TLFም ጋር ሳይቀር TLFዎችን በተኙበት እምሽክ አድርገው በልተው) ያ ምስኪን የትግራይ ህዝብ አዎ! በጦርነት ተለብልቧል። አዎ! ያ ምስኪኑ የትግራይ ህዝብ ደምቷል። አዎ! ያ ምስኪን የትግራይ ህዝብ የቅርብ ጎረቤቱ ከሆነው ወገኑና ሥጋው ከነበረው የኤርትራ ህዝብ ጋር ሳይቀር ደም ተቃብቶ  ተለያይቷል። አዎ! ያ ትሁትና ምስኪን ወገናችን የትግራይን ህዝብ፣ ወያኔዎች ከሁሉም ጋር ሊያናክሱት ብዙ ደክመዋል፣ ሰርተዋል ዛሬም የዶለቱበትን እየነገሩን ነው። ወይ ነዶ! ታዲያ ወያኔና ስብሃት ነጋ ዛሬም አይደለም የትግራይን ህዝብ የኢትዮጵያንም ህዝብ ”ነጻ” አድርገነዋል እያሉ ከበሮ በሚደልቁበት ወቅት፣ ያንን ግፍንና በደልን የሚፈራውን የሚሸሸውን የትግራይን ህዝብ (እስከ ዛሬም) ቀፍድደው፣ አሰረውት እንደሚገኙ የሚታወቅ ነው። ስብሃት ነጋና ድርጅቱ ወያኔ ይህንን በጦርነት ተፈጥረው በጦርነት የማደጋቸውን ባህሪ፣  የትግራይ ህዝብ በነጻነት እንዲናገር ቢፈቅዱለት ኖሮ ”ለእንተ ነው ይሄን ሁሉ ተጋድሎ ያደረግነው” ሊሉትና

ከትግራይ ህዝብ ፊት ቆመው ሊናገሩት አይቻላቸውም። ግን የታሰረ ህዝብ ነውና ድርጊታቸውን በአድምሞ ከመመልከት በቀር ምንስ ሊያደርግ ይቻለዋል? የትግራይ ህዝብማ ምን ያድርግ? ምንስ ሊያደርግ ይጠበቅበታል? እንኳን ያኔ ዛሬም ድረስ እኮ በወያኔ ሰንሰለት እንደታሰረ ነው! ዛሬም በወያኔ በመያዣነት፣ እንደሰው፣ እንደ ህዝብ ሳይሆን እንደ ንብረት እንደ እቃ የተያዘ ህዝብ። እንደ ኢትዮ አቆጣ ከ1968-እስከ አሁን ድረስ 31 ዓመት ሙሉ በወያኔ መያዣነት የሚገኝ ህዝብ። አቦ! እነኝህን ሰዎች እኮ ጨካኞች ናቸው ስንል ያልሆኑትን አይደለም፤ ጨካኝ የምንላቸው! ጭካኔና ክፋት በወያኔ አለቆች ላይ እግራቸውን ዘርግተው ተንሰራፍተውባቸዋል። ለዚህም ነው ያን ኩሩ ህዝብ፤ ያን ኢትዮጵያዊነቱን ከምንም በላይ በኩራትና በፍቅር እየተጀነነ፤ ሲናገረው ውሎ ቢያድር ሳይሰለቸው እንዲያውም ከሱ በላይ ኢትዮጵያዊነት ላሳር የሚመስለውን ቅን ህዝብ ነው እኮ ዛሬ ስብሃት ነጋና ወያኔዎች፣ ኢትዮጵያዊ እንዳልሆነ አድረገው ሊነግሩን አረፋ ሲደፍቁ የምናያቸው! እንኳንስ የታሪካችን መሰረት የሆነውን የትግራይን ህዝብ ቀርቶ የኤርትራን ህዝብ ከ30 ዓመት በላይ በጦርነት ውስጥ እንዲኖር አድርገው ፋታ ሳይሰጡት፣ እንደባከነ ሲኖር ኖሮ፣ ይኸውና ዛሬ "እደሜ ለእኛ ሥልጣን ማማ ላይ ደርሰናልና በኋላቀሯ ኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ሥር ወድቀህ ለረጅም ዓመታት በጦርነት ስትማቅቅ ኖረሃልና ዛሬ የራስክን ሀገር ፈጥረህ የራስክን ባንዲራ ታውለበልባለህ ብለው" የኤርትራን ህዝብ እንደ ህዝብ ምን መከራ ላይ እንዳስቀመጡት ስናይ በእጅጉ ህመማችን ከባድ ነው። ይህንን ሁኔታ የትግራይ ህዝብና መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እያየውና ዓለም እየተመለከተው ያለን ነገር፣ ዛሬ ስብሃት ነጋ መጥቶ ዋ! "ህገ-መግሥታችንን" ብትዳፈሩት በማለት ይህንን በመያዣ የያዙትን መከረኛ የሆነውን ወገናችንንና ስጋችንን የትግራይ ህዝብ "ገንጥለን እኛ ከሠራናት ኤርትራ ጋር ልንቀላቅለው እንችላለን"ብሎ ሊያስፈራራን ይሞክራል። እንኳንስ ለሙቅ ለገንፎም አንደነግጥ ተብሏልና ይሄ "የትግራይ ትግሪኝ ሪፑብሊክ" ጨኸትና አቋም ዛሬ የተፈጠረ ይመስል ድንገት በሕልሙ እንደታየው አስመስሎ ሊደነፋ ከጅሏል። ይህ የማስፈራሪያ አዋጅ ደግሞ በጅምላ ለሁሉም ማለቱ ብቻ ሳይሆን ዛሬም በውጭ ያሉ የዋህ የሆኑ የትግራይ ህዝብ ተወላጆችን ነገሩ እንዲህ ነውና እኔን አትራቁኝ አድኑኝ፣ ከእኔና ከትግራይ ህዝብ ምረጡ ብሎ አማራጫቸውን አጥብቦ ማስቀመጡ ነው። በቅሎ አባትሽ ማነው ቢሏት ፈረስ አጎቴ ነው አለች የተባለው ተረት ወያኔንና የወያኔን አለቆች በትክክል ይገልጻቸዋል። በዚህ የሲቪሊቲ ሩም ውስጥ እንደነ ሆርን (ኒክ ኔም) ዓይነት የዋህና ቅን የሆነ ወንደሜ አይነት፤ ብዙዎችም በቁጣ ተነሳስተው፣ በወቅቱ ስብሃት ነጋን የጠይቁት ጥያቄዎች ምን ነበሩ? ጠያቂዎችስ እንማን ናቸው?....

ይቀጥላል